# ምዕራፍ 8

# መስመሮችና ቀላል ምስሎች

## 8.1 ቀጥታና ጥምዝ መስመሮች

### የቡድን ሥራ 1

በየቡድናችሁ በመሆን የሚከተሉትን ተወያዩባቸው:: የተስማማችሁበትን ሃሣብ ለመምራችሁ አቅርቡ::

1. ረዥም ክር ውሰዱና አንዱን ጫፍ አንዳችሁ ሌላውን ጫፍ ሌላው ጓደኛችሁ ይዛችሁ ሳይበጠስ በአየር ላይ ወጥሩት:: ምን አይነት መስመር አገኛችሁ?



2. ከመኖሪያ ቤታችሁ እስከ ትምህርት ቤታችሁ የመጣችሁበት መንገድ ምን ዓይነት ነው? ጠመዝማዛ ወይስ ቀጥታ?
3. በመጫዎቻ ሜዳ ውስጥ ሁለት ትንንሽ ድንጋዮችን ለምልክት አኑሩ:: በምልክቶቹ መሀል ያለው ርቀት በአንዳችሁ 5 እርምጃ ይሁን:: በሁለቱ ምልክቶች መካከል በእንጨት መሬት ለመሬት አስምራችሁ አገናኙ:: አሁን ያገኛችሁት ጥምዝ ወይስ ቀጥታ መስመር ነው?

ከላይ ካከናወናችኋቸው ሥራዎች ስለ መስመር ምን ተገነዘባችሁ? የተስማማችሁበትን ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡

## የክፍል ሥራ

1. አሁን በየደብተራችሁ ገጽ ላይ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሁለት ነጥቦችን አድርጉ፡፡ እነዚህንም ነጥቦች ወ እና በ በማለት በሚከተለው ሁኔታ ሰይሙ፡፡




በማስመሪያችሁ ጠርዝ ተጠቅማችሁ ሁለቱን ነጥቦች በእርሳስ ወይም በእስክሪቢቶ አገናኙ፡፡




ይህ መስመር ቀጥታ መስመር ይባላል፡፡

የሚከተሉትን መስመሮች ተመልከቱ፡፡




ከነዚህ መስመሮች የትኞቹ ቀጥታ መስመሮች ናቸው? ጥምዝ የሆኑትስ የትኞቹ ናቸው?

2. አሁን ደግሞ ሁለት ነጥቦች በሚከተለው መልክ ደብተራችሁ ላይ በመሳል አሳዩ፡፡ ሀ ና ለ ብላችሁ ሰይሟቸው፡፡




እነዚህን ሁለት ነጥቦች በስንት መስመሮች ማያያዝ ትችላላችሁ?

ከመስመሮቹ መካከል ስንቶቹ ቀጥታ መስመሮች ናቸው?

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

**መልመጃ**

1. ከሚከተሉት መስመሮች ጥምዝ የሆኑትን ለዩ፡፡

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

ሠ. 

ረ. 

2. በደብተራችሁ ላይ ሁለት ጥምዝና ሁለት ቀጥታ መስመሮችን ሳሉ፡፡

© MoE FDRE Ethiopia
Not to be republished

## 8.2 ቀላል ምስሎች

### የቡድን ሥራ 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸው፤ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ወይም የሰራችሁትን ለመምህራችሁ

1. ቀጥለው ያሉትን ምሥሎች ተመልከቱ፡፡ የሚከተሉትንም ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡




ሀ. የሒሳብ መጽሐፋችሁ ቅርፅ ከነዚህ ምስሎች የትኛውን ይመስላል?

ለ. የክፍላችሁ ወለል ጠርዝስ ከየትኛው ምስል ጋር ይመሳሰላል?

ሐ. በመኖሪያችሁ አካባቢ ከነዚህ ምስሎች ጋር የሚመሳሰሉ ነገሮች ካሉ ዘርዝሩዋቸው፡፡

መ. ወረቀት ወይም ክላሴር በመጠቀም ከላይ ያሉትን ምስሎች አስመስላችሁ ቆርጣችሁ አውጡ፡፡

ሰ. የማስመሪያ ጠርዝ እንዲሁም በሳንቲም ዲናር ጠርዝ በመታገዝ ከላይ የተሰጡትን ምስሎች አስመስላችሁ ሳሉ፡፡

**አስተውሉ** ከላይ በተሰጠው የቡድን ሥራ የተሰጡት ሦስቱም ምሥሎች ስም አላቸው፡፡

በምስል ሀ የሚታየው ጐነ ሦስት ይባላል፡፡

በምስል ለ የሚታየው ጐነ አራት ይባላል፡፡

በምስል ሐ የሚታየው ክብ ይባላል፡፡

# የማጠቃለያ መልመጃ

1. ከሚከተሉት ምስሎች መካከል የትኞቹ ጐነ ሦስት፣ የትኞቹ ጐነ አራት እና የትኞቹ ክብ እንደሆኑ ለዩ።




2. በደብተሮቻተሁ ላይ ሁለት የጐነ ሦስት ምስሎች፣ ሁለት ጐነ አራት ምስሎች እና ሁለት የክብ ምስሎችን በመሳል አሳዩ።

3. ነጠብጣቦችን በማያያዝ የሚገኘውን ምስል በመለየት ግለጹ።



